በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ለሁሉም ጊዜ አለው

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com

***<u>ቦታ፦</u>*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ጥር ፬ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# <u>ለሁሉ ጊዜ (ዘመን) አለው</u>

- ***<u>መክብብ 3፡1-8</u>*** "ለሁሉ ዘመን አለው፥ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው። ለመወለድ ጊዜ አለው፥ ለመሞትም ጊዜ አለው ለመትከል ጊዜ አለው፥ የተተከለውንም ለመንቀል ጊዜ አለው ለመግደል ጊዜ አለው፥ ለመፈወስም ጊዜ አለው ለማፍረስ ጊዜ አለው፥ ለመሥራትም ጊዜ አለው ለማልቀስ ጊዜ አለው፥ ለመሳቅም ጊዜ አለው ዋይ ለማለት ጊዜ አለው፥ ለመዝፈንም ጊዜ አለው ድንጋይን ለመጣል ጊዜ አለው፥ ድንጋይንም ለመሰብሰብ ጊዜ አለው ለመተቃቀፍ ጊዜ አለው፥ ከመተቃቀፍም ለመራቅ ጊዜ አለው ለመፈለግ ጊዜ አለው፥ ለማጥፋትም ጊዜ አለው ለመጠበቅ ጊዜ አለው፥ ለመጣልም ጊዜ አለው ለመቅደድ ጊዜ አለው፥ ለመስፋትም ጊዜ አለው ዝም ለማለት ጊዜ አለው፥ ለመናገርም ጊዜ አለው ለመውደድ ጊዜ አለው፥ ለመጥላትም ጊዜ አለው ለጦርነት ጊዜ አለው፥ ለሰላምም ጊዜ አለው።"
- ***<u>ኤፌ 5፡15 - 20</u>*** "እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ፤ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ። ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ። መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፤ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤ ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ።"
- ***<u>ሉቃ 12፡16 - 21</u>*** "ምሳሌም ነገራቸው እንዲህ ሲል፦ አንድ ባለ ጠጋ ሰው እርሻ እጅግ ፍሬያም ሆነችለት። እርሱም፦ ፍሬዬን የማከማችበት ስፍራ አጥቻለሁና ምን ላድርግ? ብሎ በልቡ አሰበ። እንዲህ አደርጋለሁ፤ ጐተራዬን አፍርሼ ሌላ የሚበልጥ እሠራለሁ፥ በዚያም ፍሬዬንና በረከቴን ሁሉ አከማቻለሁ፤ ነፍሴንም። አንቺ ነፍሴ፥ ለብዙ ዘመን የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ፤ ዕረፊ፥ ብዪ፥ ጠጪ፥ ደስ ይበልሽ እላታለሁ አለ። እግዚአብሔር ግን። አንተ ሰነፍ፥ በዚች ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ሊወስዱአት ይፈልጓታል፤ ይህስ የሰበሰብኸው ለማን ይሆናል? አለው።"፡፡

# ለሁሉ ጊዜ (ዘመን) አለው

## *የትምህርቱ ዓላማ*

- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ።" *ኤፌ 5፡16፡፡* እንዳለን ከክርስትና አንጻር የጊዜን ዋጋና ትርጉም ፣ ጊዜን በአግባቡ የመጠቀምንና የመምራትን እንዲሁም ለመንፈሳዊ ሕይወታችን የመመደብን አስፈላጊነት መረዳት፡፡

## *ሀ. ጊዜ ምንድር ነው?*

- ከ እስከ ተብሎ የተገደበ ነገሮች የሚከናወኑበት ሂደት ነው፡፡
- በቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት እንደተጠቀሰልን ጊዜ የተሰጠን ዕድል ነው፡፡
- ጊዜ ሊጠፋ ወይም ሊያልፍ ስለሚችል በግድ በአግባቡ መጠቀም ይገባናል፡፡
- ጊዜአችንን የምንጠቀመው እንዴት ነው? ለእግዚአብሔር በቂ ጊዜ እንሰጣለን?

## *ለ. ጊዜ ያለ አድልዎ ለሁሉም እኩል ተሰጥቷል፡፡*

- ጊዜ ከእግዚአብሔር ለሰው ሁሉ የተሰጠ ዕድል ነው፡፡
- እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ የጊዜን ስጦታ እኩል ሰጥቷል፡፡ የተሰጠውንም ጊዜ በአግባብ መጠቀም ወይም አለመጠቀም ደግሞ የሰው ኃላፊነት ነው፡፡
- በምድር ያለች ዕድሜአችን ለአጭር ጊዜ ስለሆነች በጥበብ ከተጠቀምንባት ለዘላለማዊ ሕይወታችን በጎ ዝግጅት አድርገናል ማለት ነው፡፡
- በከተሞች ታላላቅ ሕንጻዎች ላይ የምንመለከታቸው የጊዜ መቁጠሪያ መሳሪያዎች ሥራቸው ጊዜውን እየቆጠሩ ማለፍ ስለሆነ አይመለሱም፡፡

# ለሁሉ ጊዜ (ዘመን) አለው

*ሐ. ሰነፍ ሰው ጊዜ የለውም*

- “ምንም ነገር ለመሥራት ጊዜ የለኝም” የሚል ሰው ከገጠመን ይህ ሰው በርግጥም ሰነፍ ሰው ነው።
- ንቁ ሰዎች ዘወትር ሥራቸውን ለመሥራት የሚያስችል ጊዜ ይፈልጋሉ። ስለዚህ ነቅተን መሥራት የሚገባንን ሥራ ለመሥራት የሚያስችል በቂ ጊዜ ማፈላለግ ይጠበቅብናል።
- እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከፈጠረ በኂላ የነገራቸው ሥራ እየሠሩ እንዲኖሩ ነው።
- የምንኩስና ሕይወት ጀማሪ የሆነውን አባ እንጦንስንም ጊዜውን ለጸሎትና ለሥራ እንዲጠቀምበት እግዚአብሔር በመልአኩ አማካይነት ነግሮታል።
- ንቁ መሆን ለአእምሮአችን፣ ለአካላችንና ለመንፈሳዊነታችን እጅግ ጠቃሚ መሆኑን እንረዳ። በተጨማሪም ንቃት ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም እጅግ ጠቃሚ ነው።

*መ. ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችሉ ቅደም ተከተሎች*

- ሕይወት በአጭርና ረጅም ጊዜ በግቦች የተሞላች ናት።
- ክርስቲያኖች በውስጣችን ያለ መንፈስቅዱስ እንደሚመራን ለየራሳችን መልካም የሆኑ ግቦች እንዲኖሩን ያስፈልገናል። መንፈስቅዱስ ይመራን ዘንድ መጸለይ አለብን።
- ግባችንንም ለመፈጸም እንችል ዘንድ በቅደም ተከተል ማዘጋጀትና ለእያንዳንዱም የሚያስፈልገውን በቂ ጊዜ መመደብ አለብን።

# ለሁሉ ጊዜ (ዘመን) አለው

## *መ. ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችሉ ቅደም ተከተሎች…*

- ለምሳሌ ለሚቀጥለው ቀን የምናስረክበው የቤት ሥራ፣ በየዕለቱም መደበኛ ትምህርታችንን የማጥናት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብና መጸለይ ቢኖርብን አስቀድመን ቅዱሳት መጻሕፍትን እናንብብ፣ ሌሎችንም ነገሮች ከማድረጋችን በፊት እንጸልይ፡፡ በመቀጠልም ለሚቀጥለው ማስረከብ የሚኖርብንን ሥራ በቂ ጊዜ ሰጥተን በተቻለን መጠን በመሥራት እንፈጽም፡፡
- የተረፈን ተጨማሪ ጊዜ ካለን መደበኛ ትምህርታችንን እናጥና፡፡
- በየሥራዎቻችን መካከልም እግዚአብሔር ጊዜአችንንና ሥራችንንም ይባርክልንና የምናጠናው ወይም የምንሠረውም በፍጥነት ግልጽ ይሆንልን ዘንድ እንጸልይ፡፡
- ለሁሉ ዘመን አለው፥ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለውና እንደ ግባችን ቅደም ተከተል ሁሉን ጊዜ ሰጥተን መጠቀም ይኖርብናል፡፡
- ፍሬያማ የሚባለው ሰው ጊዜውን በአግባቡ የሚጠቀምና ለጸለሎት፣ ለሥራ/ለጥናት፣ ለእረፍት/ለእንቅልፍ፣ ለመናገር የሚስማማውን ጊዜ በአግባቡ የሚያውቅ ነው፡፡

## *ሠ. የጊዜ አሥራት ማውጣት*

- *<u>በሚል 3፡7-10</u>* እግዚአብሔር ከሁሉም አሥራት እንድንሰጥ ጠይቆናል፡፡
- አስቀድሞ እንደተገለጠው እግዚአብሔር ጊዜን ስጦታ አድርጎ የሰጠን በመሆኑ እኛም ከሰጠን ጊዜ በየቀኑ 2.4 ሰዓት ለእግዚአብሔር መስጠት አለብን፡፡
- ታዲያ አሥራታችንን እየሰጠነው ነው? በዚሁ የአሥራት ጊዜ እንጸልይበታለን፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን እናነባለን፣ ቤተ ክርስቲያንንና ችግረኞችን እናገለግልበታለን?
- በየቀኑ ከ24 ሰዓት ውስጥ 2.4 ሰዓቱ ለእግዚአብሔር የምንሰጠው የአሥራት ጊዜ እንደሆነ እንረዳ፡፡

# ለሁሉ ጊዜ (ዘመን) አለው

## *ረ. ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም - በዋዛ ፈዛዛ ማሳለፍ*

- አንድን ነገር በጊዜው ሳይሠሩ በመቅረት ማስተላለፍ ክፉ የሰው ጠላት ነው፡፡ ሰው ዘወትር በባከነ ሰዓት ለመጠቀም የሚሞክር ሰው ያደርገዋል፡፡
- በባከነ ሰዓት ለመጠቀም የሚሞክር ሰው በድንገት የመጡ መሠራት የሚገባቸውን ነገሮች ማከናወን የሚያስችል ዝግጅት የሌለው የተሠሩትንም ነገሮች ለመገምገምና ለማሻሻልም የማይቻለው ነው፡፡
- ጊዜን ማባከን በአግባብ አለመጠቀም ዘወትር ለመንፈሳዊ ህይወታችንም አደጋ ነው፡፡
- ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም በንስሐ ሕይወት ቀጠሮ እየቀጠረ እያፈረሰ… ሰውን ዘላለማዊ ሕይወትን ወደ ማጣት ሊያደርሰው ይችላል፡፡
- ቀጠሮን አለመጠበቅ የጠፋው ልጅ "ተነሥቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁና። አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥" ***ሉቃ 15፡18፡፡*** እንዳለው ያለውን ዕድል ያሳጣል፡፡

## *ሰ. ትክክለኛውን ጊዜ ብቻ መጠቀም*

- ነገሮችን ለመፈጸም መጣደፍ ሳይሆን ነገሮቹን በአግባቡ በማጥናት ወደ ተግባር መግባት አስፈላጊ ነው፡፡
- የሚመለከቱንንና ተዛማጅ ነገሮችን ሁሉ በአግባብ ስንረዳቸው ብቻ ወደ ተግባር መግባት ይኖርብናል፡፡ ይህ እስኪሆንም በትዕግሥት እንጠብቅ፡፡
- የጌታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት እንኳ "ነገር ግን ***የዘመኑ ፍጻሜ*** በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ" **ገላ 4፡4** እንዳለው ትክለኛ ጊዜን የጠበቀ ነው፡፡ የነቢያቱ ትንቢት፣ ጨለማው የጸና መሆኑ፣ እመቤታችን መወለድዋ፣ … ሁሉ ሲፈጸም ተወለደ፡፡
- 

# ለሁሉ ጊዜ (ዘመን) አለው

***ምን ተማርን?***

- ግባችንንና ቅደም ተከተሎቹን በማስተካከል ጊዜን ስለመጠበቅ
- የታቀደውን ጊዜ በዋዛ ፈዛዛ ማጥፋት ተገቢ አለመሆኑን፣ በተገቢው ጊዜ ወይም ትክክለኛው ጊዜ ላይ ተግባራችንን ማከናወን እንዳለብን
- አስቀድመን በማቀድ ጊዜአችንን በጥበብ እንጠቀም
- ለዓለም ከሆኑ ነገሮች እረፍት በማድረግ ለእግዚአብሔርና ለመንፈሳዊ ነገሮች ጊዜአችንን መስጠት እንዳለብን፡፡
- እግዚአብሔርን፣ ቤተ ክርስቲያንንና ቤተ ሰቦቻችንን እንዲሁም ሌሎችን ማገልገል የምንችልበት ጊዜ ሊኖረን እንደሚገባ፡፡

***ጊዜን በአግባብ ተቆጣጥሮ የመጠቀም ጥቅሞች***

- በፍጥነት ሥራን ለመሥራት መቻል፣ ስህተቶችን ለመቀነስ መቻል፣ ከቀጠሮ በፊት ሥራን ማድረስ መቻል
- የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ፣ የሥራችንን ጥራት ማሻሻል፣ ጫናን መቀነስ፣ ለነገሮች አስቀድሞ ዝግጁ መሆን
- ሥራው ወይም ጉዳዩ የሚጠይቀውን ፍላጎት ማሻሻል፣ ጊዜንና ሕይወትን አመጣጥኖ መምራት መቻል
- ጊዜ ሰው ሊጠቀመው የሚችለው ታላቁ ቁምነገር ነው፡፡
- የአንድ ሰው ዕድሜ 74 ዓመት ነው ብለን ብናስብ ይኽን ዕድሜ እንዴት ተጠቅመነው እንደምናልፍ ቀጥሎ በተቀመጡት የማሳያ ስሌቶች እንመልከት፡-

| | |
|---|---|
| 1. እንቅልፍ » 25 ዓመት | 6. ራስን መንከባከብ » 1.5 ዓመት |
| 2. ሥራና/ት/ቤት » 17 ዓመት | 7. ሕክምና/ሆስፒታል » 5 ዓመት |
| 3. ምግብ መመገብ » 7 ዓመት | 8. ቴሌቪዥን » 6 ዓመት |
| 4. መታጠቢያ መጠቀም » 1.5 ዓመት | 9. ሰዎችን ጥያቃ » 2 ዓመት |
| 5. ጉዞ ወይም መንገድ » 2.5 ዓመት | 10. መዝናናት/የምንወደውን ማድረግ » 6 ዓመት |

- ከላይ የተቀመጡት መንፈሳዊ ነገርን ሳይጨምሩ ሲሰሉ 74.5 ዓመት ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም መንፈሳዊነትን ዘንግቶ ስላልሆነ አጠቃቀማችን ጉድለቱ መስተካከል ያሻዋል፡፡

# <u>በዘመናችን ጊዜን ከሚያጠፉብን ነገሮች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው</u>

- ዋዛ ፈዛዛ/ ሥራን በጊዜው አለመሥራት
- ኢሜይል/ኢንተርኔት/ፌስ ቡክ/ ትዊተር/…
- ዕቅድ አልባ መሆን
- ለምንሠራው ሥራችን ቅደም ተከተል አለማዘጋጀት
- የምንሠራውን ሥራ በአቅማችን መወሰን አለመቻል
- ሐሜት
- ለምንሠራው ሥራ ፍላጎት ማጣት
- በተለያዩ ነገሮች መጎዳት ወይም የሞራል መነካት
- አደናቃፊ ነገሮች
- ስለ ምንሠራው ነገር በቂ መረጃ አለማግኘት
- ሥራን ለሌሎች አለማካፈል ወይም ከሰጡ በኋላ ያለ በቂ ምክንያት መውሰድ
- የስብሰባዎች መብዛት
- ግባችንን አለማወቅ
- የማይሆንልንን ነገር አልችለውም ማለት አለመቻል
- ንዴት ወይም ብስጭት
- በአንድ ጊዜ በርካታ ሥራዎችን ለመሥራት መሞከር

“ለሁሉ ዘመን አለው፥ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው።ለመወለድ ጊዜ አለው፥ ለመሞትም ጊዜ አለው ለመትከል ጊዜ አለው፥ የተተከለውንም ለመንቀል ጊዜ አለውለመግደል ጊዜ አለው፥ ለመፈወስም ጊዜ አለው ለማፍረስ ጊዜ አለው፥ ለመሥራትም ጊዜ አለው ለማልቀስ ጊዜ አለው፥ ለመሳቅም ጊዜ አለው ዋይ ለማለት ጊዜ አለው፥ ለመዝፈንም ጊዜ አለው ድንጋይን ለመጣል ጊዜ አለው፥ ድንጋይንም ለመሰብሰብ ጊዜ አለው ለመተቃቀፍ ጊዜ አለው፥ ከመተቃቀፍም ለመራቅ ጊዜ አለውለመፈለግ ጊዜ አለው፥ ለማጥፋትም ጊዜ አለው ለመጠበቅ ጊዜ አለው፥ ለመጣልም ጊዜ አለው ለመቅደድ ጊዜ አለው፥ ለመስፋትም ጊዜ አለው ዝም ለማለት ጊዜ አለው፥ ለመናገርም ጊዜ አለው ለመውደድ ጊዜ አለው፥ ለመጥላትም ጊዜ አለው ለጦርነት ጊዜ አለው፥ ለሰላምም ጊዜ አለው። ለሠራተኛ የድካሙ ትርፍ ምንድር ነው?እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ይደክሙበት ዘንድ የሰጣቸውን ጥረት አይቻለሁ።ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው እግዚአብሔርም ከጥንት ጀምሮ እስከ ፍጻሜ ድረስ የሠራውን ሥራ ሰው መርምሮ እንዳያገኝ ዘላለምነትን በልቡ ሰጠው።ሰው ደስ ከሚለውና በሕይወቱ ሳለ መልካምን ነገር ከሚያደርግ በቀር መልካም ነገር እንደሌለ አወቅሁ።ደግሞም ሰው ሁሉ ይበላና ይጠጣ ዘንድ በድካሙም ሁሉ ደስ ይለው ዘንድ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።እግዚአብሔር ያደረገው ሁሉ ለዘላለም እንዲኖር አወቅሁ ሊጨመርበት ወይም ከእርሱ ሊጐድል አይቻልም እግዚአብሔርም በፊቱ ይፈሩ ዘንድ አደረገ።አሁን ያለው በፊት ነበረ፥ የሚሆነውም በፊት ሆኖ ነበር እግዚአብሔርም ያለፈውን መልሶ ይሻዋል።ደግሞም ከፀሐይ በታች በፍርድ ስፍራ ኃጢአት፥ በጽድቅም ስፍራ ኃጢአት እንዳለ አየሁ። እኔም በልቤ። በዚያ ለነገር ሁሉና ለሥራ ሁሉ ጊዜ አለውና በጻድቅና በኃጢአተኛ ላይ እግዚአብሔር ይፈርዳል አልሁ።” ***<u>መክብብ 3:1-17።</u>***

ይቀጥላል...

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org